June 12, 2006

# ከኢትዮጵያ ብሔራዊ አንድነት አርበኞች ግንባር ማዕከላዊ ኰሚቴ የድርጅቱን ተግባር ባጐደፉ አባላት ላይ ያወጣ ልዩ መግለጫ!

የኢትዮጵያ ሕዝብ ከወደቀበት የወያኔ ግፍ አገዛዝ ለመላቀቅ በጋራም ሆነ በተናጠል ከሚደረጉ የነፃነት ትግሎች አንድ ዓላማ ያለን በውስጥ ሆነ በውጭ ካሉ ታጋይ ድርጅቶች ጋር የኢትዮጵያ ብሔራዊ አንድነት አርበኞች ግንባር በውህደት ሆነ በግንባር መሥራት የግል ጥቅማቸውን የሚቀንስባቸው መስሎ ሰለታያቸው የድርጅታችንን የአመራር አካል ልዩ ስም በመሰጠት ያለአግባብ በማጉደፋቸውና በግንባሩም ፕሮግራም ላይ በውስጣችን ሆነው ችግር በመፍጠራቸው የኢትዮጵያ ብሔራዊ አንድነት አርበኞች ግንባር መመሪያና የመተዳደሪያ ደንብ አንቀጽ 13 በሚያዘው መሠረት…

1ኛ/ ዶ/ር በቀለ ሞላ ከዋሽንግተን ዲስ

2ኛ/ አቶ መላኩ ሥዩም ከካናዳ ከኢ.ብአአግ የሥራ አመራር ታግደዋል።

ዶ/ር በቀለ ሞላ ዋና ዓላማቸው በስዊዲን ስቶክልም የተደረገውን ኅብረት ምሥረታ መቃወም ሲሆን፤ በኋላ ግን ሽፋን በመፈለግ የኢ.ብአአግ አመራር አባላት ላይ አሉባልታና ድርጅታዊ ያልሆኑ የተሳሳቱ መግለጫዎችን በድርጅታችን ስም አውጥተዋል። ቀጥለውም የአርበኞች ልሳን የሆነውን የኢትዮጵያ ብሔራዊ አርበኞች አንድነት ግንባር የራዲዮ ሥርጭት እንዲተጓጎል አድርገዋል።

አቶ መላኩ ሥዩም በካናዳ የኢ.ብአአግ ተወካይ ሆነው ሲሰሩ በቆዩበት ዘመን በካናዳ የኢ.ብአአግ ደጋፊዎች የሆኑትን ታጋዮች ስም ዝርዝር ለማዕከላዊ ኰሚቴ እንዲያቀርቡ ተጠይቀው ለማስረከብ ባለመፈለጋቸው ከካናዳ የሚገኙት አባላት ምንም ዓይነት የፖለቲካ ሆነ የኢኰኖሚ ድጋፍ ለማግኘት አለመቻሉ ከአቶ መላኩ ጋር ለመሥራት ከፍተኛ ችግር ድርጅታችን ገጥሞታል። በካናዳ የሚገኙ የኢ.ብአአግ አባላት ብዙ የገንዘብ አስተዋጽኦ እንዳደረጉ ብናምንም እስከዛሬ ድረስ ማዕከላዊ መምሪያው ምንም አስተዋፅኦ አላየም። ገንዘቡ ወዴት እንደደረሰም አያውቅም።

የግንባሩ መሥራች ኢንጂነር ቅጣው ለኢትዮጵያ ያላቸው ራዕይ ተዳፍኖ፤ ዛሬ ደግሞ በኢንጂነር ቅጣው ስምና ዝና በመጠቀም የግል ንግድና ትርፍ ለማካበት የሚያደርጉት ሙከራ እጅግ በጣም አዛዝኖናል።

በዚህ አጋጣሚ የዋሽንግተን ዲሲ ጽ/ቤት ሆነ ፖስታ ሳጥኑ ጉዳዩ እስኪጣራ ጊዜ ድረስ ስለተዘጋ በጊዜአዊ አድራሻ **ENUPF NORTH AMERICA HEADQUARTER**
**P O Box 984, ATLANTA GA 30085**
**TEL. (404) 394-4321 FAX. (770) 414-0061** መሆኑን እንገልጻለን

ድል ለኢትዮጵያ ሕዝብ!
ኢትዮጵያ በእግዚአብሔር ቸርነትና በሃቀኛ ልጆችዋ የተባበረ ትግል ነፃ ትወጣለች!
ኢትዮጵያ ብሔራዊ አንድነት አርበኞች ግንባር ሊቀመንበር
ኰ/ል አሥራት ቦጋለ